## ምድብ አራት (ከ7ኛ — 9ኛ) ክፍል

## 29 ኛ ሳምንት

# ኅብስተ ሕይወት

**ዓላማ**

- የክርስቶስ ሥጋና ደም የመቀበልን አስፈላጊነት መማር።

**የሚጠና ጥቅስ**

- ***" ሥጋውን ካልበላችሁ ደሙን ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ህይወት የላችሁም "*** ዮሐ. 6፣53

**ምንባብ** ዮሐ.6

**መግቢያ**

- ክርስቶስ ብዙ ህዝብ በተሰበሰበበት በቅፍርናሆም ስለ ኅብስተ ህይወት አስተማረ።
- በዚህ ትምርታችንም ህብስተ ህይወት(የህይወት ኅብስት)ምን?እንደሆነ እንማራለን ጥቅሙንም ከዚያ ውጭ የመኖርን ውጤት እናያለን።
- ትምህርቱ ብዙ ሰዎች ክርስቶስ ስለሚሰራቸው ድንቅና ተዓምራት ይከተሉት ነበር።
- አንድ ቀንም የገሊላ ባህር ወደሚባለው ሲጓዝ ብዙ ህዝብ እንደተለመደው ተከትሎት መጣ።በዚያ ቀንም ከሁለት ዓሣ እና አምስት እንጀራ አበርክቶ አምስት 5000 (ሺ.ህ) ህዝብ መገበ።
- ከዚህ በኂላ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ወደ ቅፍረናሆም በጀልባ ሄደ ህዝቡም መሄዱን ሲያውቁ በሚቀጥለው ቀን በንጋት ተከትለው ወደ ቅፍረናሆም መጡ።
- ጌታችንን ሲያገኙትም መቼ እንደመጣ ጠየቁት እርሱም ***"የምትፈልጉኝ እንጀራ ስለበላችሁና ስለጠገባችሁ እንጂ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም።"*** አላቸው።
- ከዚያም ***"ለሚጠፋ መብል አትስሩ ፤ ነገር ግን ለዘላለም ህይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ፤ እርሱን እግዚአብሔር አብ አትሞታልና"*** ሕዝቡም ***"የእግዚአብሔርን ሥራ እንድንሰራ ምን እናድርግ?"*** አሉት።ጌታችንም የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው።አላቸው።
- እውነተኛ እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ አባቴ ነው…የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሠጥ ነውና አላቸው።
- ሕዝቡም ጌታሆይ ***"ይሄን እንጀራ ዘወትር ስጠን"*** አሉት። ጌታም መልሦ ***"የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም።"***
- በእኔ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው።***"የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ"*** አባቶቻችሁ በበረሃ መና በሉ ሞቱም።ከሠማይ የወረደ ኅብስት ይህ ነው ከርሱ የሚበላም አይሞትም።***ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፡***ከዚህ እንጀራ የሚበላ ለዘለዓለም አይራብም ለዘላለም ይኖራል እንጂ፤ለዓለም ሕይወት እንዲሆን የምሠጠው ኅብስት ሥጋዬን ነው።
- የሰውን ልጅ ሥጋውን ካበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም።ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።አባቴ እንደላከኝ፣እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን፣ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል።ከሠማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው።***"ከዚህ የሚበላም ለዘለላም ይኖራል።"***
- የተከተሉት ህዝብም እንዴት ሥጋውን ልንበላ ይሰጠናል ብለው አጉረመረሙ። ደቀመዛሙርቱም ይህ ለመቀበል ከባድ ነው አሉት። ብዙ ሕዝብም ወደ ኂላው ተመለሰ። ስለዚህ ጌታ ደቀመዛሙርቱን ***"እናንተስ መመለስ ትፈልጋላችሁ?"*** አላቸው።
- ስምዖንም መልሶ ***"ወዴት እንሄዳለን ፣አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፣ እኛስ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ አምነናል አውቀናልም"*** ብሎ መለሰለት።
- ደቀመዛሙርቱም ተከተሉት የክርስቶስን ሥጋና ደም ለመቀበልም (በጸሎተ ሐሙስ) የመጀመሪያዎቹ ሆኑ።

**ማጠቃለያ፡-**

በጌታችን ትምህርት መሠረት ሥጋውንና ደሙን ካልተቀበልን ሕይወት የለንም። "የሰውን ልጅ (የክርስቶስን) ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ ሕይወት የላችሁም።" ዮሐ. 6፣53 የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ለመቀበል ማዘጋጀት አለብን።

በዚህም፡-

- ሕይወት ይኖረናል
- የዘለላም ሕይወት እናገኛለን
- በእርሱ እንኖራለን እርሱም በእኛ ይኖራል።

ይቆየን……

- አንዳንዴ የመጻሕፍትን ትምህርትና መልእክት መረዳት ሊያቅተን ይችላል ነገር ግን እምነት ሆነን፤
- እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ***"ጌታ ሆይ ወዴት እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ"*** ብለን በትህትና ስንቀርብ፣ ወደ እውነተኛው መረዳት መገለጥ እንደርሳለን።ደቀመዛሙርቱ በትህትና ተከትለውት ነው ከመለኮታዊ ምሥጢር ለመከፈል የበቁት።

**የሙከራ ጥያቄዎች፡-**

1. ክርስቶስ በገሊላ ባሕር የፈጸመው ተዓምር ምን ነበር? ሕዝቡስ ለምን ተከተሉት
2. እውነተኛው የሕይወት መብል /ኅብስተ ሕይወት/ ምንምድነው?
3. ክርስቶስ በፍቅርናሆም ላስተማረው ትምህርት ደቀመዛሙርቱ ምን አሉ?
4. የጌታችንን ቅዱስ ሥጋና ደም በመጀመሪያ የተቀበሉት እነማን ናቸው?
5. ቅዱስ ቁርባን እንቀበላለን?
6. ከቅዱስ ቁርባን ውጪ መኖር ምን ያመጣል?

**ይቆየን፡፡**